

የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

2018 በጀት አመት የአፈጻጸም ሪፖርት

ሰኔ 2018

አዲስ አበባ

ማውጫ

1.አጠቃልሎ /Executive Summary/ 3
2.መግቢያ 4
3.የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች 5
ራዕይ 5
ተልዕኮና 5
እሴቶች 5
4.የሪፖርቱ ዓላማ 5
5.የሪፖርቱ አስፈሊጊነት 5
2.1የተቋም ግንባታና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ከማሳደግ አኳያ 6
ተግባር 1. የተቋሙ አፈጻጸም ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲተገበሩ ማድረግ በቁጥር 1፤ 11
2.2የከተማ መልካም አስተዳደር ችግር መፍታት፣ የአቤቱታ መወሰንና ማስፈጸም አቅም ማጎልበት እና ተቋማዊ የቅንጅት፣ የትብብርና የድጋፍ አሰራር ስርዓት ማሻሻል፤ 11
2.3የዕቅድ/ሪፖርት ዝግጅት፣ የኢንሺቲቭ ስራዎች አሰራር ሥርዓትን ማጎልበት 14
ክፍል ሶስት 17
3. የተቋሙ ዓበይት ተግባራት/የቁልፍ አፈፃፀም አመላካቾች (Key Performance Indicators) አፈፃፀም 18
3.1. የጥናት፣ ምርምር እና የፕሮሞሽን ስራዎችን በማጠናከር የኢንቨስትመንት ፍሰትን መጨመር፤ 18
3.1.1. የኢንቨስትመንት ጥናቶችን በማሳደግ፣ ለኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ 18
3.1.2. የተጠናከረ የፕሮሞሽን ስራበመስራት የመረጃ ተደራሽነትን ወደ 4300 ማድረስ፤ 19
3.2. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰራርን ማሳደግ 20
3.2.1. የኢንቨስትመንት ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶችን ወደ 6110 ማሳደግ፣ 20
3.2.2. የዉጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ለሥራ ፈቃድ ጥያቄ ምላሽ መስጠት 21
3.2.3. የመረጃ ዴክስ፣ ጥሪ ማዕከልና መዝገብ ቤት አገልግሎት ማሻሻል፤ 22
3.3. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመረጃ ጥራት፣ የክትትልና ድጋፍ ሽፋን ማሳደግ 22
3.3.1. አዲስ እና ነባር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመረጃ ጥራት ወደ 23,719 ማሳደግ፣ 22
3.3.2. በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ላይ የክትትል ስርዓቱን ሽፋን ወደ 27,071 ማሳደግ፤ 22
3.4. ለፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ የድጋፍ ስርዓት መዘርጋት 23
3.4.1. የድጋፍና የማመቻቸት ተግባር (facilitation) ውጤታማነትን 100% ማሳደግ፣ 23
3.4.2. የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ፍቃድ እና የገቢ ግብር እፎይታ ድጋፍ 1260 ማሳደግ፤ 24
3.4.3. ማምረት ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ፕሮጀክቶች ቁጥር ከ157 ወደ 250 ማሳደግ፣ 25
3.5. የአገልግሎት አሰጣጥ እና ማበረታቻዎች አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል፣ 26
3.5.1. የአገልግሎት አሰጣጥ ትክክለኛነትን ቁጥጥር ስራን ከ1299 ወደ 1320 ማሳደግ፣ 26
3.5.2. የማበረታቻ ድጋፎች ለታለመላቸዉ ዓላማ መዋላቸዉን ቁጥጥር ሽፋን ወደ 264 ማሳደግ፣ 26
ክፍል አራት 26
4.በመደመር መንግስት ዕይታ፤ የዘርፎች እመርታ በተመለከተ 27
ክፍል አምስት 29
5. በአፈፃፀም ሂደት የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች፤ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች 29
4.3. የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍቶተች 29
4.3.1. የነበሩ ጠንካራ ጎኖች 29
4.3.2. የነበሩ ክፍተቶች 30
4.4. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 30
4.4.1. 5.2.1 ያጋጠሙ ችግሮች 30
4.4.2. 5.2.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 30
4.5. ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች። 31
4.6. የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች 30
ክፍል ስድስት 31
5. ማጠቃለያ 32

ክፍል አንድ

1.1. አጠቃልሎ /Executive Summary/

አዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በአዋጅ 84/2016 የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ የ2018 በጀት ዓመት የተቋሙን ተልእኮ በአግባቡ ለመወጣት በሚያስችል መልኩ የአመቱን የልማት ዕቅድ በማቀድ ከኮሚሽኑ ፈጻሚ አካላት፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻና ያገባኛል ባዮች ጋር ተግባብቶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡

በዚህም ኮሚሽኑ በእቅድ የተያዙ ዋና ዋና ስራዎች ላይ በማተኮር የተሸለ ተቋማዊ ውጤት ለማስመዝገብ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በተለይ የ90 ቀን የንቅናቄ እቅድን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የእቅድ ዝግጅትና ትውውቅን በአግባቡ በመምረት ከተቋሙ ሰራተኛ እስከ ባለድርሻና የተቋሙ ባለጉዳይ ድረስ የጋራ ማድረግና መግባባት የተቻለበት ሂደት በበጎ የሚታይ ነው፡፡ ተቋሙ መሰረታዊ የሆኑ ኢንቨስትመንት ነክ ጥናቶችን በማጥናትና በመጠቀም ጠንካራ የፕሮሞሽን ስራዎችን በተለያዩ አግባቦች የተሰራበት መረጃዎችን በአግባቡ ለተጠቃሚ በማድረስ ባለሀብቱ ወደ ኢንቨስትመንቱ እንዲሳብ የተጠናከረ ስራ በመስራት ከፍተኛ ቅጥር ያለው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ለነባር ባለሀብቶች ጠንካራ ድጋፍና ክትትል በማድረግና በህግ የተፈቀደላቸውን ማበረታቻዎች ተጠቅመው ፕረጀክቶቻቸውን ወደ ስራ የማስገባትና ማስፋፊያ እንዲያደርጉ በማድረግ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው እንዲገባና ለበርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች የስራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ፕሮጀክቶች በኤክስፖርትና በተኪ ምርቶች እንዲሰማሩ በማገዝ ከተማችን ብሎም ሀጋራችን የሚደርሰውን የምንዛሬ ጫና ላይ አስተዋፅኦ ማበርከት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በህግ የተፈቀዱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉ ለማድረግ ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ተላልፈው የተገኙ ፕሮጀክቶች ላይም አሰራሩን የጠበቀ እርምጃዎች ተውስዷል፡፡

ባጠቃላይ ኮሚሽኑ የተጀመሩ የለውጥና መልካም አስተዳደር የማስፈን እና ቅንጅታዊ ስራዎችን በማጠናከር፣ አገልግሎቶች የኦንላን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ፍትሃዊ፣ ግልጽና ተደራሽ በሆነ መንገድ መስጠት፤ መልካም ግንኙነቶችን ቀጣይነት ለማረጋገጥና አሰራር ሆነው እንዲቀጥሉና፤ ለቀጣይ ያለውን ጥንካሬ የሚያጎለብትና ድክመቶችን በሚያርም መልኩ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

1.2. መግቢያ

አዲስ አባበ ከፍተኛ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግባት፣ በርካታ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት የሚገኙባት፣ በአንፃሩ ደግሞ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ የሚከተል ማህበረሰብ የከተመባት ከተማ በመሆኗ ይህን ታሳቢ ያደረገ ከአስር አመትና አምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድን መሰረት ያደረገ የኮሚሽኑን የ2018 በጀት አመት እቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል።

ኮሚሽኑ በ2018 በጀት አመት የበጀት አመቱን እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር የገባ ሲሆን በዋናነት የከተማ አስተዳደሩ ከለያቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ በማበረታታት እና በማስፋፋት የከተማውን ብሎም የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን፣ የእድገቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ፣ የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማጠናከር እና በአገር ኢኮኖሚ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማፋጠን፣ የወጪን ግድን ለማስፋፋት በሚሰሩ ስራዎች ላይ ነው። በዚህም በዓመቱ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ለ4900 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠ፣ ፕሮጀክቶችን በመከታተልና በመደገፍ 261 ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉ፣ ለ7611 የከተማችን ነዋሪዎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት መጠን እና የተሳትፎ መስክ በማስፋት የዕውቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ጠንካራ የግንኙነት ስረዓት በመዘርጋት ከኮሚሽኑ የበላይ አመራሮች እስከ ፈፃሚ ድረስ ያለውን ሰንሰለት በአደረጃጀት በማስተሳሰርና ቀጣይነት ያለው የውስጥና የመስክ ክትትልና ድጋፍ ስረዓት በመዘርጋት ከሰራተኛውም ሆነ ከባለሀብቱ ጋር ውጤታማ ግንኙነትና የተሸለ ስራ መስራት ተችሏል።

የአፈፃፀም ሪፖርቱ በ6 ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን፣ በክፍል 1 አጠቃሎ፣ መግቢያ፣ የሪፖርቱ አላማ፣ የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የያዘ ነው። በክፍል 2 ደግሞ የተቋሙ ቁልፍ ግቦችና ተግባራት አፈፃፀም በጥልቀት የተተነተነበት ክፍል ነው። በክፍል 3 አበይት ተግባራት አፈፃፀም የተዳሰሰበት ሲሆን በክፍል አራት በመደመር መንግስት ዕይታ፤ የዘርፎች እመርታ በተመለከተ፣ ክፍል አምስት በአፈፃፀም ሂደት የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች፤ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች እና ክፍል ስድስት ማጠቃለያ የተዳሰሰበት ነው። በ2018 በጀት አመት እቅድ በድርጊት መረሀ ግብር በተተነተነው መሰረት የበጀት አመቱ ዝርዝር አፈፃፀም ተዘጋጅቶ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1.3. የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

ራዕይ

በ2022 አዲስ አበባን በኢንቨስትመንት ተመራጭ እና ቀዳሚ በማድረግ የአፍሪካ ብልጽግና ተምሳሌት ሆና ማየት።

ተልዕኮና

የከተማዋን እምቅ ሃብት በማጥናትና በማስተዋወቅ ጥራት ያለዉ ኢንቨስትመንትን በመሳብ እና ቀጣይነቱን በማረጋገጥ የምጣኔ ሃብት፣ የሥራ እድል፣ የወጪ ንግድ ገቢን ማሳደግ።

እሴቶች

- ✓ ተጠያቂነት
- ✓ ተቋማዊ ሃላፊነት
- ✓ የአገልግሎት ጥራት
- ✓ ግልጽና አሳታፊነት
- ✓ መልካም ስብእና

1.4. የሪፖርቱ ዓላማ

ኮሚሽኑ በ2018 በጀት አመት ተቋማዊና ከተማዊ ሀላፊነቱን ለመወጣት በበጀት አመቱ በእቅድ ሊተገብረው ከያዘው አንፃር ያለበትን ደረጃ በግልፅ ለመለካት፣ ባጠቃላይ ከነበረው አፈፃፀም ትምህርት ወስዶ ለቀጣይ አቅም ለማዳበርና መረጃውን በአግባቡ አደራጅቶና ሰንዶ ለመጠቀምና ለሚመለከታቸው ተቋማት መረጃውን ማድረስ ነው።

1.5. የሪፖርቱ አስፈሊጊነት

ተቋሙ ከበጀት አመቱ ዕቅድ አንጻር አፈፃፀሙ የደረሰበትን አፈፃፀም በማመላከት፣ ዋና ዋና ጥንካሬዎችን ለማስቀጠል እና ከአፈፃፀም አንጻር ያጋጠሙ ጉድለቶች ለማረም የሚያስችል ትምህርት ለመውሰድ የተሄደበትን ርቀት በሚያሳይ መልኩ በማስቀመጥ ለተጠሪ ተቋማት ተቋሙ ያለበትን ደረጃ ለማሳየት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ የአፈፃፀም ሪፖርት ማደራጀትና ለማቅረብ በማስፈለጉ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

2. የተቋሙ ቁልፍ ተግባራት አፈፃፀም

2.1 የተቋም ግንባታና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ከማሳደግ አኳያ

2.1.1 አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል እርካታን ከማሳደግ አንፃር

ተግባር 1- በተቋም የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እንዲሰጡ ማድረግ በመቶኛ 100%፤ በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች በየቀኑ በባለሙያ ይመዘገባሉ፣ በቡድን መሪ ከተቀመጠላቸው የቢፒአር ስታንዳርድ አንፃር እየተጠመሩ በየሩብ አመቱ 4 ጊዜ ተቋማዊ ስታንዳርድ ንፅፅር ተሰርቷል። በዚህም፡-

- የተለዩ አገልግሎቶች 23፣
- በስታንዳርድ የተሰጡ አገልግሎቶች 5፣
- ከስታንዳርድ በላይ (አወንታ) የተሰጡ አገልግሎቶች 18 ናቸው።

ተግባር 2- በአገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋሉ ሌብነትና የብልሹ አሰራር ማክሰሚያ ስርዓት በመዘርጋት መተግበር በመቶኛ 100%፤ በአገልግሎት አሰጣጥ የሚታዩ የሌብነትና ብልሹ አሰራር ምንጮች በተቋም ደረጃ ተለይተው ለምንጮቹም ማክሰሚያ እቅድ ተዘጋጅቶ ከአመራርና ከሰራተኛ ጋር የጋራ ተደርጎ ወደ ተግባር ተገብቷል፤ በዚህም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ይከሰቱ የነበሩ ብልሹ አሰራሮችን መቆጣጠር ተችሏል።

ተግባር 3- አገልግሎት በስታንዳርድ የማይሰጡ አካላትን ተጠይቂ ማድርግ በመቶኛ 100%፤ በየደረጃው ያለ አመራር በየቀኑ ጥብቅ ክትትል እየተደረገ አገልክሎቶች በስታንዳርድና ከስታንዳርድ በላይ እየተሰጡ ስለሆነ ተጠያቂ የሆነ አካል የለም፣

2.1.2 ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር አገልግሎቱን ማሻሻልን በተመለከተ

ተግባር 1- በተቋሙ ምቹ የመስተንግዶ ስርዓት በመዘርጋት እንግልት እንዲቀንስ ማድረግ እቅድ 100% አፈፃፀም 100%፤

- በሁሉም አገልግሎት መስጫ የስራ ክፍሎች የተገልጋይ ማረፊያ ወንበር እና ጠረጴዛ የተዘጋጀ መሆኑ በተለይ በበጀት ዓመቱ ቀደም ብሎ ከነበረው 119 የባለጉዳይ ወንበር በተጨማሪ 43 የባለጉዳይ ወንበሮች እና የሃላፊ ጠረዛና ወንበሮችን በማስገባት

አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ በአንድ ጊዜ 159 ተገልጋዮች የሚስተናገዱበት የቢሮው ውስጥ አደረጃጀት በማስተካከል ተደራጅቷል፣

- በተቋሙ ለውስጥ እና ለውጭ ተገልጋዮች የላበራሪ አገልግሎት፣ የካፍቴሪያ አገልግሎት፣ ደረጃውን የጠበቀ መፀዳጃ ቤት በማመቻቸት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፣
- የህፃናት ማቆያ አገልግሎትን ስታንዳርዱን ለማሻሻልና እንደገና ለማደራጀት የኢትዮጲያ ደንና ዱር አራዊት ባለስልጣን ከፍተኛ አመራሮችና የኮሚሽናችን ከፍተኛ አመራሮች የመግባቢያ የስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል፣ አስፈፃሚ ኮሚቴም ተዋቅሮ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡



- የሶሻል ኮሚቴን እንደገና በማጠናከር ሁሉንም የተቋሙ ሰራተኞችን አባል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣ የሽማች ሱቅ ለማቋቋም ከሌሎች የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የልምድ ልውውጥ ተደርጎ የማደራጀት ስራ በመሰራት የሰራተኛ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ግበዓት የማቅረብና ሰራተኛው ተጠቃሚ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- የተቋሙ ሰራተኞች ጤናማነት ለማሻሻል የሚያስችል የስፖርት ኮሚቴ ተቋቁሞ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡









ተግባር 2- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተገልጋዮች የአገልግሎት ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችሉ አማራጭ መንገድ አገልግሎት መስጠት፣

ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተገልጋዮች ያማከለ አገልግሎቶችን ለመስጠት የልዩ ድጋፍ ዴስክ በማቋቋም፣ የልዩ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያም ጭምር በመወከል ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፣ በተጨማሪ የኤልኢዲ አገልግሎቱን የልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ በተለይ ማየት ለተሳናቸው የኦዲዮ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል።

2.1.3 ብዙሃን መገናኛ አውታሮችን በመጠቀም የአገልግሎት ውጤታማነት ማረጋገጥ

ተግባር 1. የሚዲያ ሽፋን በመስጠት የተገልጋይና የአገልጋይ መድረክ በመፍጠር እንዲሳተፉ ማድረግ በቁጥር 1፣

በበጀት አመቱ የሬድዮ ፕሮግራም በመጠቀም መረጃዎችን ማሰራጨትና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችል ስራ ተሰርቷል። በዚህም በበጀት ዓመቱ 35 ሳምንታዊ የሬድዮ ፕሮግራሞችንና 9 የቴሌቪዥን ፕሮግራም በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አየር ላይ በማዋል የአገልግሎት ግልፀኝነትና መረጃን ለተጠቃሚ የማድረስ ስራዎች ተሰርተዋል።

ተግባር 2. ከተገልጋይ በተሰጡ ግብዓቶች መሰረት አገልግሎት እንዲሻሻል ማድረግ በመቶኛ እቅድ 100% ክንውን 100%፣ በመድረክ ከተገልጋይ የተነሱ አስተያየቶች በጎ ምላሽ እና የሚበረታቱ ናቸው። አገልግሎት እንዲሻሻል የተሰጠ አስተያየት የለም።

3.1.4. ተቋማዊ አቅም ግንባታ ስርዓት በመዘርጋት የሰራተኛውን የመፈጸም አቅም ማጎልበት፤

ተግባር 1. ተቋማዊ የክፍተት ዳሰሳ ስራ በመስራት የሰራተኞችን የባህሪያዊና የቴክኒካል ብቃት ክፍተት መመላት፣ በተቋሙ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በመስራት የማስፈፀሚያ እቅድም ተዘጋጅቷል። በእቅዱ መሰረት 11 ስልጠናዎችንና በወቅታዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም 2 በድምሩ 13 ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ተጠንቶ ሰነድ ተዘጋጅቷል፦

- የሰራተኛ አቅምን ማሳደግና የተሻለ አገልግሎት መስጠት አስችሏል፤
- ተቋማዊ የአመራርና የሰራተኛ መነቃቃት ፈጥሯል፤
- አጠቃላይ አፈፃፀም አወንታዊ ተፅኖ አሳድሯል፤

ተግባር 2. ተቋማዊ የዕውቀት አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤

የእውቀት ስራ አመራር በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የእውቀት አስተዳደር ማኑዋል ተዘጋጅቶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የአቅም ልየታ ስራ ተሰርቶ ወደ ተግባር ተገብቷል።

ተግባር 3. ወርቃማ ሰኞ/አብሮነት/ መድረክ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ማድረግ፣

ወርቃማ ሰኞ የግንኙነት አግባቡን በጠበቀ መልኩ እየተካሄደ ይገኛል፣ በበጀት ዓመቱ ያለምንም መቆራረጥ 48 ጊዜ ተካሂዷል። በዚህም በርካታ የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮችን ያካተተ ልምድ፣ ተሞክሮና እውቀት የተላለፈበትና በተቋሙ የእርስ በእርስ ግንኙነትን እያጠናከረ መድረክ መሆን ችሏል።



ወርቃማ ሰኞ/የአብሮነት ሳምንት/

3.1.5. ተቋማዊ ውጤታማነት በማሻሻል የሰራተኛና ተገልጋይ እርካታ ከማሳደግ አኳያ

ተግባር 1. የቀነሰ የተቋሙ የሰራተኛ ቅሬታ፤ (100% መቀነስ)፤

በተቋሙ የሰራተኛ የቅረታ አቀራረብ ስረዓቶች በተቋሙ የቅሬታ ኮሚቴ ቅሬታውን በቀላሉ ለመስማትና ምላሽም ለመስጠት የሚያስችል ስረዓት የተዘረጋ ቢሆንም የቀረበ ቅሬታ የለም፡፡

ተግባር 2. የሰራተኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት መስራት (ወደ 85% ማሳደግ)

የሰራተኛ እርካታ ዳሰሳ ጥናት በበጀት አመቱ 85% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 83.7% እርካታን ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ ይህም ባለፈው አመት ከነበረው 65.3% የእርካታ ደረጃ 18.4% ማሳደግ ተችሏል፤

ተግባር 3. የተቋሙ የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳ ጥናት መስራት (ወደ 100% ማሳደግ)

የተገልጋይ እርካታ 100% ለማድረስ ታቅዶ 94.7% በማድረስ ባለፈው አመት ከነበረው 93.4% የእርካታ ደረጃ 1.3% ማሳደግ ተችሏል፤

3.1.6. በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሰጡ አገልግሎቶች ውጤታማነትን ከማሻሻል አንፃር

ተግባር 1. በተቋም ደረጃ በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሠጡ አገልግሎቶች የመለየት ስራ መስራት፤ በተቋሙ አጠቃላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች 23 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሰጡ አገልግቶች 18 ሲሆኑ በአግባቡ በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፤ በዚህም

- የተገልጋይን ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት ብክነት ቀንሷል፡፡
- መተቋሙ የተገልጋይና ባለሙያ ንክኪን በመቀነስ የሙስና ተጋላጭነትን ቀንሷል፡

- በተቋሙ የመረጃ አያያዝን በማዘመን የአገልግሎት አሰጣጡን አሻሽሏል።

ተግባር 2. ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ ማድረግ፤ በተቋሙ እና በከተማ አስተዳደሩ የአንድ ማዕከል የሞሶብ አገልግሎት አገልግሎቶችን በኦንላይን በመስጠት ተደራሽ ተደርጓል፤

3.1.7. የአዳዲስ አሰራርና ፈጠራ ልምዶችን ከማሳደግ አኳያ

ተግባር 1. የተቋሙ አፈጻጸም ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲተገበሩ ማድረግ በቁጥር እቅድ 1 ክንውን 1፤

- በተቋም አገልግሎት ላይ የአግልግሎት ጥያቄና ምላሽ የሚሰጥ ጎግል ፎርም በመፍጠር የአይሲቲ ቴክኒክ ድጋፎችን በዚህ አግባብ እየተደገፉ ይገኛል፤

ተግባር 2. የተፈጠሩ አዳዲስ ስራዎች እንዲቀመሩ በማድረግና በተቋም ደረጃ በመግባባት ለስራ ክፍሎች የማስፋት ስራ መስራት፤ በተቋም ደረጃ ያሉ የስራ ክፍሎች እንዲጠቀሙበት ተደርጓል።

ተግባር 3. አዳዲስ ስራዎች በመተግበራቸው የተገኙ ተጨባጭ ውጤቶች ማስፋት በመቶኛ 100%፣ የሰራተኛ የወረቀት ብክነት ቀንሷል፣ ጊዜንና ጉልበትን ቆጥቧል።

2.2 የከተማ መልካም አስተዳደር ችግር መፍታት፣ የአቤቱታ መወሰንና ማስፈጸም አቅም ማጎልበት እና ተቋማዊ የቅንጅት፣ የትብብርና የድጋፍ አሰራር ስርዓት ማሻሻል፤

2.2.1. የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ቅሬታን የመቀነስ አሰራር ማሳደግ፤

ተግባር 1. በህዝብ የሚነሱና በየደረጃው የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና የቅሬታ ምንጮች በቁጥር 1 ጊዜ፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአግባቡ ተለይተው የአመቱ እቅድም ተዘጋጅቶ በእቅድ የተመራ ተግባራዊ ስራዎች ተሰርተዋል።

ተግባር 2. የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመቶኛ 100%፣

<u>የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች</u> 4 ናቸው እነዚህም፡-

- የተገልጋይ የፋይሎች የዳታ እርማት ችግር፣
- ከአዋጅና ደንብ ውጭ የሚሰጡ የውጭ ዜጎች ቅጥር ችግር፣
- ከአሰራር ውጪ የታደሰ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚጠይቁ የፌደራል ተቋማት ችግር፣
- የኦንላን አገልግሎት ለመስጠት በሰርቨር ችግር ምክንያት የሲስተም መቆራረጥ፣

<u>የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች 4 (ሁሉም) ተፈተዋል፤</u>

ተግባር 3. በተገልጋይ ለቀረበ ቅሬታና አቤቱታ አሰራሩን ጠብቆ የተሰጠ ምላሽ በመቶኛ እቅድ 100% አፈፃፀም 100%፣ አገልግሎቱ ላይ የሚስተዋሉ ቅሬታ እንዳይኖር ክትትል የማድረግ ስራው በየእለቱ ተሰርቷል። በአፈጻጸም ወቅት የቀረበ ቅሬታ የለም፡

ተግባር 4. በተገልጋይ በአንድ ማዕከል ላይ ለቀረበ ቅሬታና አቤቱታ የተሰጠ ምላሽ በመቶኛ፣ በሁሉም ቀናት ያለምንም የጊዜ ገደብ አገልግሎቱ እየተሰጠ ስለሆነ የአንድ መዓከል ተብሎ የተለየና የተሰጠ አገልግሎት የለም፣

2.2.2. የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ማስፈን፤

ተግባር 1. የተወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነት አፈፃፀም እቅድ 100% አፈፃፀም 100%፣

<u>ከውስጥ ሰራተኛ</u>

- ✓ በበጀት ዓመቱ ሌብነትና ብልሹ አሰራር ውስጥ ገብተው የተገኙ 2 ፈፃሚዎች ላይ ማለትም ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ አያይዘው የተገኙት ላይ መረጃ ተጣርቶ እርምጃም ተወስዷል።
- ✓ ከቅርብ ሀላፊ ፍቃድ ውጭ በመቅረትና በማርፈድ የ36 ሰዎች 61,564.09 ብር ተመላሽ ተደርገዋል።
- ✓ ያለአግባብ የስልጠና አበል የወሰዱ የ15 ሰራተኞች አበል 11,778 ተመላሽ ደርጓል።

<u>ከተገልጋይ</u>

በመስክና በቢሮ በተዳሰሱ ፕሮጀክቶች ላይ የተገኙ ግኝቶችና የተወሰደ እርምጃ፤

በቁጥጥር ከተዳሰሱ ፕሮጀክቶች ውስጥ 59 ፕሮጀክቶች የወሰዱትን የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ለታቀደለት ዓላማ ባለማዋላቸው እርምጃ ተወስዷል፣

በዚህም፡-

1. የ32 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘና የወሰዱትን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ለጉምሩክ መረጃ የተላከ፣
2. የ10 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃዳቸው የታገደ፣
3. ለ17 ፕሮጀክቶች የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው፣
4. 53,386,047.90 ብር የመንግስት ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ተደርጓል፡

ተግባር 2. የተወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነት አፈፃፀም በመቶኛ 100%፣ የተወሰነ ውሳኔ የ2 ሰራተኛ የስራ ስንብት ሲሆን ሁለቱም በውሳኔው መሰረት ከስራ የታገዱ፣ ያለአግባብ የስልጠና አበል የወሰዱ የ15 ሰዎች የወሰዱት አበል እንዲመልሱ ተደርጓል በተጨማሪም የ36 ሰራተኞች ያልሰሩበት ታስቦ ተመላሽ ተደርጓል።

ተግባር 3. በየደረጃው በአፈፃፀም ሂደት ለታዩ ችግሮች ተጠያቂነት ማረጋገጥ እቅድ 100% አፈፃፀም 100%፣

በውስጥ ሰራተኛ በሁለት ሰራተኞች በቀረበባቸው የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ክስ ላይ የስራ ስንብት ውሳኔ ተላልፏል። የስልጠና አበልና ከሀላፊ ፈቃድ ውጪ ያረፈዱ ሰራተኞች ያልሰሩበት ታስቦ ተመላሽ የማድረግ እርምጃ ተወስዷል።

በሌላ በኩል ገተገልጋይ በተገኘ ግኝት መሰረት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ፈቃድ የተሰረዘና የወሰዱትን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ለጉሙሩክ መረጃ የተላከ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማገድ፣ የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠትና የመንግስት ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ተደርጓል።

2.2.3. የህዝብ፣ ሲቪል ማኅበራትና የግል ሴክተር ተሳትፎ ስርዓትን ከማሳደግ አንፃር፤

ተግባር 1. ተቋም ተኮር ሲቭል ማህበራት የተለዩ ብዛት እቅድ 3 ክንውን 3 ማህበር ተለይተዋል፣ የሲቭክ ማህበራትን ያካተተ የመማክርት ጉባዔ በማቋቋም ስራዎችን መስራት ተችለዋል።

ተግባር 2. በጋራ ፍላጎት መሠረት የተዘጋጀ መድረክና ተሳትፎ 2 መድረክ ክንውን 3፣

የሲቭክ ማህበራትን ያካተተ የመማክርት ጉባዔ 3 መድረኮች ተደርገዋል የመስክ ስራዎችም ታይተዋል።

2.2.4. ተቋማዊ ውጤታማነትን ከማሳደግ አንፃር፤

ተግባር 1. በመልካም አስተዳደር ችግርና ቅሬታና አቤቱታ ምንጮች ዙርያ የተደረገ ጥናት ብዛት በቁጥር 1፤

የበተቋሙ የመልካም አስተዳደር ችግርና ቅሬታና አቤቱታ ምንጮች ለመለየት የልየታ ኮሚቴን በማዋቀር በአግባቡ የተለየ ሲሆን በዋናነት ችግሮችን ለመለየት የተገልጋይ መድረኮችን፣ የመስክ ድጋፍና ክትትል ምልከታ ወቅት የተገኙ ችግሮች፣ በዳሰሳ ጥናትና

በስራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን መነሻ በማድረግ የችግር ልየታ ሰነድ በማዘጋጀት ከሰነዱ በመነሳት የተቋሙን የመልካም አስተዳደር እቅድ ማዘጋጀት ተችሏል።

ተግባር 2. የጥናት ውጤቱ ጥቅም ላይ ለማዋል የተፈጠረ የስልጠና እና ስርፀት መድረክ ብዛት በቁጥር እቅድ 1 ክንውን 1፤

በተቋሙ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መድረክ ለአጠቃላይ አመራርና ሰራተኛ ተሰጥቷል። በተፈጠረው መድረክና አሰራሮችን በመፈተሽ ችግሮቹን መፍታት ተችሏል።

2.2.5. ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት እና አተገባበር ማሳደግ በተመለከተ

ተግባር 1. በስታንዳርዱ መሰረት በተቋሙ የተለዩና በጋራ ያቀዱ ተቋማት ብዛት 12 ከክንውን 12 አፈፃፀም 100%፤ ቀደም ብሎ በእቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም የቅንጅት ስራዎች በከተማ አስተዳደር ደረጃ በክላስተር እንዲመራ በተፈጠረው አደረጃጀት መሰረት ስራዎች እየተመሩ ይገኛሉ።

ተግባር 2- እቅዱን ለማሳካት በአፈፃፀም ሂደት የተደረጉ የጋራ ግምገማዎች በመድረክ እቅድ 4 ክንውን 2፤ በክላስተር እንዲመራ በተፈጠረው አሰራር መሰረት የተሰራ፣ በዚህ የተጠቀሰው አሀዝ ቀደም ብሎ በበጀት አመቱ በጀመሪያ የተሰራ።

2.3 የዕቅድ/ሪፖርት ዝግጅት፣ የኢንሸቲቭ ስራዎች አሰራር ሥርዓትን ማጎልበት

2.3.1. በተቋማት የስራ አመራር ስርዓት ውጤታማነትን ከማሻሻል አኳያ፤

ተግባር 1- ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድ/ክለሳ ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ በቁጥር እቅድ 2 ክንውን 3 አፈፃፀም 100%፤

የተቋሙ የበጀት አመቱ እቅድ የ6 ወር የተከለሰ እቅድ ከዘርፉ፣ ከዳይሬክተር፣ ከቡድን፣ እንዲሁም በተዋረድ ከሰራተኛ ጋር ተናባቢ በሆነ መልኩ መረጃው እየተሰበሰበ የተቋሙ የእቅድም ሰነድ በአግባቡ ተዛጋጅቷል።

ተግባር 2. ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ በቁጥር እቅድ 12 ክንውን 12 አፈፃፀም 100%፤ የየወሩ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል።

ተግባር 3. የተቋም እቅድ እና አፈጻጸም እስከ ሰራተኞች ያለው ተናባቢነት በቁጥር እቅድ 4 ክንውን 4 አፈፃፀም 100%፤

የበጀት አመቱ እቅድና አፈፃጸም ከዘርፉ ዕቅድ እቅድና አፈፃጸም ከዳይሬክተሮች ከቡድን መሪዎች እንዲሁም በተዋረድ ከሰራተኛ ጋር ተናባቢ በሆነ መልኩ መረጃው እየተሰበሰበ የተቋሙ የእቅድና የአፈፃፀም ሰነዶች በየሩብ ዓመቱ እየተገመገሙ በአግባቡ ተዛጋጅተዋል።



ተግባር 4- ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ለማረጋገጥ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተገኘ ውጤት፣ በቁጥር እቅድ 4 ጊዜ ክንውን 4 ጊዜ አፈፃፀም 100%፤ የድጋፍና ክትትል ስራው የመስክ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ደረጃ እና በቢሮ ውስጥ የስራ ክፍሎች አፃፀምና አሰራር ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ መልሶችም ተሰጥተው ማስተካከያዎች ተደርገዋል።





ተግባር 5- በየሩብ ዓመት አፈጻጸም ከዘርፍና ከስራ ክፍሎች ጋር በጋራ ስራ መገምገምና ውጤታማ ማድረግ፣ በቁጥር እቅድ 4 ጊዜ ክንውን 4 ጊዜ ሲሆን አፈፃፀም 100%፤

የተቋሙ የየሩብ ዓመቱ አፈፃፀም ከዘርፍና ከስራ ክፍሎች እንዲሁም ከሰራተኛ ጋር በጋራ ተገምግሟል ፤

ተግባር 6- በተለያዩ ዘዴዎች የተቋምን እቅድና አፈጻጸም ለባለ ድርሻ አካላትና ለተገልጋይ በማስተዋወቅና ማሳተፍ፣ በቁጥር 2 ጊዜ ክንውን 2 ጊዜ ሲሆን አፈፃፀም 100%፤ የተቋሙን እቅድና አፈፃፀም ከባለድርሻ አካላትና ከተመረጡ የተቋሙ ተገልጋዮች ጋር የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡



2.3.2. የተቋም በጎ አድራጎት እና ኢንሸቲቪ ሥራዎችን ከማጎልበት አንፃር

ተግባር 1. የአቅመ ደካማ ቤተሰቦችን ቤት ማደስ፣ እቅድ በቁጥር እቅድ 3 ቤት ክንውን 3 ቤት ሲሆን አፈፃፀም 100%፤ በዚህም በጎ አድራጊ ባለሀብቶችን በማፈላለግና ከከተማ አስተዳደሩ የእድሳት ድጋፍ የሚፈልጉ ቤተሰቦችን በመውሰድ የእድሳት ስራውን ከበጎ ፍቃደኛ ግለሰቦች ጋር በማገናኘት ተሰርቷል፡፡



ተግባር 2. የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከልና መንከባከብ፣ እቅድ በቁጥር እቅድ 2000 ችግኝ ክንውን 2050 ሲሆን አፈፃፀም 102.5%፤ በበጀት አመቱ በሁለት ዙር 124 አመራሮች፣ ሰራተኞችና ባለድርሻ አካላት በሁለት ዙር በማሳተፍ ተተክሏል፡፡ እንክብካቤን በተመለከተ በአጠቃላይ አመራርና ሰራተኛ ጥቅምት ወር ላይ ተሰርቷል፡፡




ተግባር 3. ወላጆቻቸውን ያጡ ወይም የገቢ አቅማቸው ደካማ በሆኑ ወላጆች ስር የሚተዳደሩ ህፃናትን መደገፍ፤ በቁጠር እቅድ 3 ህፃናት ክንውን 4 አፈፃፀም +100%፤ ለ4 ህፃናት በወር የሚደረግ ወርሃዊ ተቆራጭ 27,879 እና የበዓላት ማዕድ ማጋራት 48,417 በድምሩ 76,296 ብር ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

ተግባር 4. ማዕድ ማጋራት እቅድ 400 ሰው ክንውን 404 በብር 1,630,050.00፣

- በተጨማሪም የኮሚሽኑ በጎ ፍቃድ ሰራተኞች ደም ልገሳ ተደርጓል፡፡





ክፍል ሶስት

2. የተቋሙ ዓበይት ተግባራት/የቁልፍ አፈፃፀም አመላካቾች (Key Performance Indicators) አፈፃፀም

3.1. የጥናት፣ ምርምር እና የፕሮሞሽን ስራዎችን በማጠናከር የኢንቨስትመንት ፍሰትን መጨመር፤

3.1.1. የኢንቨስትመንት አማራጭ ጥናቶችን ወደ 5 ማሳደግ፣ ለኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

ተግባር 1. የከተማዋን አማራጭ የኢንቨስትመንት መስኮችን በጥናት በውጭ አቅም /አውትሶርስ/ መለየት እቅድ 1 ክንውን 1 አፈፃፀም 100%፣ ስራው በውስጥ አቅም የተሰራና በከተማችን ያለ እምቅ የኢንቨስትመንት አቅምን ለባለሀብቶች ለማስተዋወቅ እንደ ግበዓት ተጠቅመንበታል።

ተግባር 2. የተሰሩ ኘሮጀክት ኘሮፋይሎች፣ እቅድ 10 ክንውን 4 አፈፃፀም 40 በመቶ፣ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክኒያት ስራውን የሚሰረው ተጫራች በጨረታ ባለመሳተፋቸው ሲሆን ከግዢ አሰራር ጋር በተያያዘ በውስን ጨረታ መመሪያ መሰረት ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ ለመስራት የግዢ ህጉ ስለሚከለክል አፈፃፀሙን ዝቅ አድርጎታል።

ተግባር 3. የተጠኑ ችግር ፈች ጥናቶች፣ እቅድ 2 ክንውን 2 አፈፃፀም 100%፣ አንደኛው በማምረቻው ዘርፍ ያሉ ዕድሎችና ተግዳሮቶች የሚልና ሁለተኛው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ውጤታማነትን ጥናት ተሰርቷል።

ተግባር 4. የተጠኑ የደንበኛ እና የሰራተኛ የእርካታ ጥናት፣ አቅድ 2 ክንውን 2 አፈፃፀም 100%፣

የሰራተኛ እርካታ ዳሰሳ ጥናት የተሰራ ሲሆን ውጤቱም በጥናቱ መሰረት 83.7% እርካታን ማስመዝገብ ተችሏል። ይህም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ማለትም 65.3% ጋር ሲነፃፀር የ18.4% ብልጫ አለው። የተቋሙ የተገልጋዮች እርካታ 94.7% በማድረስ ባለፈው አመት ከነበረው 93.4% የእርካታ ደረጃ 1.3% ማሳደግ ተችሏል፤

3.1.2. ዓላማ 2. የተጠናከረ የፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት የመረጃ ተደራሽነትን ከ4215 ወደ 4300 ማድረስ፤

ተግባር 1. አንድ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ እቅድ 1 ክንውን 1 አፈፃፀም 100%፣ ፕሮሞሽን ስትራቴጂውን ተግባረዊ ለማደረግ የተለያዩ የውይይት ሂደቶችን በማድረግ ለተቋሙ ከፍተኛ አመራር ለግምገማ የቀረበ ሲሆን በቀጣይ ለሚመለከታቸው ባለድርሻና ያገባኛል ባዮች በማስተችት ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል፡፡

ተግባር 2. ለደንበኞች የምክር እና መረጃ አገልግሎት መስጠት እቅድ 4,300 ክንውን 4,323 ደንበኞች ተሰጥቷል አፈፃፀሙም 104 በመቶ ይሆናል፣

የምክርና መረጃ አገልግሎቱ የተሰጠው ወደ ተቋሙ ለሚገለገሉ ደንበኞች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዝ ሲሆን በከተማው ውስጥ በሚገኙ የንግድ መዳረሻ ቦታዎች ማለትም ሞሎች፣ በመርካቶ ገበያ ማዕከላት ላይ ቤትለቤት (በእካል)፣ በክፍሉ የመረጃ ባለሙያና ሰራተኞች በስልክ እንዲሁም በሶሻል ሚዲያ (በቴሌግራም እና በዋትስ አፕ) በመጠቀም የተዘጋጁ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንንና መመሪያዎችን ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር 3. በራስ አቅም እና በሚዘጋጁ ኤግዚብሽኖች ላይ በመሳተፍ ማስተዋወቅ እቅድ 4 ክንውን 5 አፈፃፀሙ 100%፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ኮሚሽን፣ በኢትዮድያ ጎብረት ሥራ ኮሚሽን እና በአዲስ አበባ ጎብረት ሥራ ኮሚሽን፣ ፊንቴክ የፈርኒቸር፣ የቤት ውበት እና የግንባታ አጨራረስ ኤክስፖ/ኤግዚብሽን እና 27ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ ኤግዚብሽን እና ባዛርና ፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አለማቀፍ ፎረም ላይ በመሳተፍ የኮሚሽኑን አገልግሎቶች ማስተዋወቅ ተችሏል፡፡

ተግባር 4. የፕሮሞሽን ቁሳቁሶችን በመጠቀም ማስተዋወቅ በቁጥር እቅድ 5500 ክንውን 5500 አፈፃፀም 100%፣


በበጀት ዓመቱ የተሰራጩት መረጃዎች በግልና በማህበር አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲያወጡ ማሟላት ላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችን የሚገልጽ፣ በግልና በማኅበር ማስፋፊያ ለሚያፈርጉ ባለሃብቶች ቅድመ ሁኔታዎችን የያዘ እና የተለያዩ የፕሮጀክት ፕሮፋይል መግለጫዎች ናቸው፡፡

ተግባር 5. ከአጋር አካላት ጋር ሁለት የኢንቨስትመንት ፎረም ማዘጋጀት እቅድ 2 ተይዞ ስራውን ለመስራት ከፋይናንስ አሰራር ጋር ተያይዞ ስራውን መስራት አልተቻለም፡፡

ተግባር 6. በኢንቨስትመንት አማራጭ እና ማበረታቻ ዙሪያ የኢንቨስትመንት የግንዛቤ እና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት እቅድ 2 ክንውን 2 አፈፃፀም 100%፣ ከንግዱ ማህበረሰብ የተውጣጡ አቅም ያላቸውን ታዳሚዎች በተገኙበት መድረክ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገብባቸውን አማራጮችን እና እድሎችን በሚመለከት የማወያየት ስራ ተሰርቷል፤

3.2. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰራርን ማሳደግ

3.2.1. የኢንቨስትመንት ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶችን ከነበረበት 5973 ወደ 6110 ማሳደግ፣



የፈቃድ ነክ አገልግሎቶች ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር

ተ.ቁ	ተግባራት	መለኪያ	የ2017 በጀት አመት አፈፃፀም	2018 በጀት አፈፃፀም	አድገት (በመብለጥ ወይም በማነስ)
1	ባለሀብቶች አዲስ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት	ቁጥር	3383	4900	45%
2	ለባለሀብቶች ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት	>>	290	346	19%
3	ባለሀብቶች ለውጥ /ማሻሻያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት	>>	387	329	-15%
4	ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት መስጠት	>>	2110	1332	-37%
5	የዉጭ ዜጋ ተቀጣሪ ሰራተኞች የሥራ ፈቃድ	>>	139	114	-18%
6	ከኢንቨስት ፈቃድ ነክ፣ ማበረታቻና ሌሎች ድጋፎች የሚገኝ ገቢን መሰብሰብ፤	በሚ.ብር	30.6	36.2	18.3%

ከላይ የፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶች በዚህ የተሰጡት አገልግሎቶች ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ውጤት የተመዘገበበት አመት ነው፡፡ በተለይም የተሰጠ አዲስ የኢንቨስትመንት ፍቃድ 45 በመቶ እድገት፣ ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ፈቃድ 19 በመቶና የተሰበሰበ ገቢ 18 በመቶ እድገት ያሳዩ ዘርፎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አሰራሮችን በማሻሻል በተለይ የኢንቨስትመንት ፍቃድ እድሳት በአዋጁ መሰረት እድሳት የሚጠይቁ ባለሀብቶችን ለማስተናገድ አሰራር ስለተበጀለት እኒዲሁም የውጭ ዜጋ ቅጥር ፍቃድ አሰጣጥ ቁጥጥር ስለተደረገባቸው ከባለፈው አመት አፈፃፀም አንፃር አፈፃፀሙ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት 37 በመቶ፣ ለውጥ /ማሻሻያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ 15 በመቶ እንዲሆም የዉጭ ዜጋ ተቀጣሪ ሰራተኞች የሥራ ፈቃድ 18 በመቶ አፈፃጸሙ ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ ማለት አሰራርና ቅድመ ሁኔታዎችን በማካተት የተሰሩ ስራዎች ኢንቨስትመንቱን ጤናማ አካሄድ እንዲኖር ይረዳዋል እንጂ ተፅኖ አለው ተብሎ አይወሰድም፡፡

3.2.2. የዉጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ለሥራ ፈቃድ ጥያቄ ምላሽ መስጠት

ተግባር 1፡- ለየዉጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ለሥራ ፈቃድ ፈላጊዎች ለ140 ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ክንውን 114 አፈፃፀም 81% ይሆናል፣ ይህም ከዚህ በፊት የሰራበት

የነበረውን የአሰራር ማሻሻያ በመደረጉ የመልካም አስተዳደርም ችግር ስለነበረበት ችግሩን በሃላፊነት ተይዞ በስራት በመጀመራችን ውጤት ዝቅ ሊል ችሏል

ተግባር 2፡- የዉጭ ዜጋ ቀጣሪዎች ጋር መድረክ በማዘጋጀት በችግሮቻቸዉ ላይ ወይይትና መፍትሄ ማፈላለግ እቅድ 4 ክንውን 4፣

ተግባር 3፡- ለዉጭ ዜጋ ቀጣሪዎች በመስክ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እቅድ 4 ክንውን 4፣

3.2.3. የመረጃ ዴክስ፣ ጥሪ ማዕከልና መዝገብ ቤት አገልግሎት ማሻሻል፤

ተግባር 1፡- የተሰረዙ ፋይሎችን በማደራጀት ለወመዘክር ማስረከብ ፡ በቁጥር ከ25,000 ፋይል፣ ክንውን 15000 ፋይል ተደራጅቶ ለወመዘክር ለማስረከብ በሂደት ላይ ያለ፡፡

ተግባር 1፡- የተገልጋይን የስልክ ጥሪ ማዕከል ማቋቋም በቁጥር 1፣ በበጀት አመቱ ያልተፈፀመ በሂደት ላይ ያለ፡

3.3. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመረጃ ጥራት፣ የክትትልና ድጋፍ ሽፋን ማሳደግ

3.3.1. አዲስ እና ነባር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመረጃ ጥራት ከ20,655 ወደ 23,719 ማሳደግ፣

ተግባር 1፡- ነባር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን 19000 መረጃ ማደራጀት ታቅዶ 19000 ተከናውኗል አፋፃፀም 1000%፣

ተግባር 2፡- አዲስ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን 4719 መረጃ ማደራጀት ታቅዶ 4693 ተከናውኗል አፋፃፀም 99%፣

3.3.2. በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ላይ የክትትል ስርዓቱን ሽፋን ከ20,999 ወደ 27,071 ማሳደግ፤

ተግባር 1፡- በሚቀርቡ አዲስ የሶስት ወርና የስድስት ወር የፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ የሚደረግ ክትትል ብዛት 4719 ታቅዶ 4683 ተከናውኗል አፋፃፀም 99%፣

ተግባር 2፡- የአፈፃፀም ደረጃቸውን ለመለየት የመደበኛ ክትትል የሚደረግባቸው ነባር ፕሮጀክቶች ብዛት 19000 ታቅዶ 19000 ተከናውኗል አፋፃፀም 1000%፣

ተግባር 3፡- በትግበራ ላይ ያሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ችግር ፈቺ ድጋፍ መስጠት የሚያስችል የመስክ ክትትል 2456 ለማድረግ ታቅዶ 2494 ተከናውኗል፣ አፋፃፀም 102%፣

በድጋፍና ክትትል ስራዎች የተገኙ ዋና ዋና ችግሮችና የተደረጉ ድጋፎች

- የመስሪያቦታ ክራይ ቤጊዜው መጨመር/መሬት ችግር 15 ፕሮጀክቶች፣
- የብድር አቅርቦት በባንኮች በኩል አለመኖር 31 ፕሮጀክቶች የሚያነሱት ችግር፣
- ከግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች 8 ፕሮጀክቶች፣
- የማምረቻ ካፒታል እቃ ብልሽት/እሳት ቸአደጋ 19 ፕሮጀክቶች፣
- የግንባታ እቃዎች ዋጋ በየቀኑ መቀያየር 4 ፕሮጀክቶች፣
- ጥሬእቃ አቅርቦት ችግር 13 ፕሮጀክቶች፣
- የገበያ ትስስር ችግር 9 ፕሮጀክቶች፣
- መስረተ ልማት/መብራት፣ ውሀ፣ መንግድ ችግር 11 ፕሮጀክቶች፣
- የፕሮጀክት ባለቤት በራሳቸው ችግር 18 ፕሮጀክቶች፣
- የውጪ ምንዛሪ ችግር 17 ፕሮጀክቶች

ኮሚሽኑ እንደየችግራቸው ከተቋማት ጋር በጋራ አሰራርን ምክነያት በማድረግ እየተፈታ ይገኛል፡፡

ተግባር 4፡- በሆቴል፣ ቱሪዝምና አይሲቲ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የክትትል ድጋፍ እቅድ በቁጥር 146 ክንውን 146 አፋፃፀም 100%፤

ተግባር 5፡- በኤክስፖርት ለተሰማሩ ባለሀብቶች የክትትልና ድጋፍ እቅድ በቁጥር 100 ታቅዶ 100 ተከናውኗል አፋፃፀም 100%፤

ተግባር 6፡- ተኪ ምርቶች ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚደረገውን የክትትል ድጋፍ እቅድ በቁጥር 650 ታቅዶ 666 ተከናውኗል አፋፃፀም 102%፤

3.4. ለፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ የድጋፍ ስርዓት መዘርጋት

3.4.1. የድጋፍና የማመቻቸት ተግባር (facilitation) ውጤታማነትን 100% ማሳደግ፣

ተግባር 1፡- የፋይናንስ፣ የብድር እና የውጭ ምንዛሬ ድጋፍ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ማድረግ፣ 100% ተከናውኗል፤ ጥያቄውን ላቀረቡ 49 ፕሮጀክት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ተግባር 2፡- የመሰረተ ልማት አውታሮች ጥያቄ (የውሃ፣ የመብራት፣ የመንገድ፣ የስልክ እና ኢንተርኔት መስመር ዝርጋታ) ድጋፍ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ፕሮጀክቶች 100% ተከናውኗል፤ ጥያቄ ላቀረቡ 3 ፕሮጀክት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ተግባር 3፡- ቀረጥ ተከፍሎባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የግንባታ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ መለዋወጫ፣ ተሸከርካሪ እና ጥሬ ዕቃዎችን ለማስገባት ለሚቀርብ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ማድረግ 100% ተከናውኗል፤ ለ395 ፕሮጀክቶች ድጋፍ ተደረጓል፡፡

ተግባር 4፡- የቴክኒክ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች ድጋፍ መስጠት ብዛት 35 ታቅዶ 35 ተከናውኗል አፋፃፀም 100%፤

ተግባር 5፡- ከአካበባቢ ጋር የሚኖራቸው ተስማሚነት የተረጋገጠላቸው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች ብዛት እቅድ 20 ክንውን 20 አፋፃፀም 100%፤

ተግባር 6፡- በድህረ- ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ተለዩ ፕሮጀክቶች ብዛት እቅድ 32 ክንውን 32 አፋፃፀም 100%፤

3.4.2. የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ፍቃድ እና የገቢ ግብር እፎይታ ድጋፍ 1260 ማሳደግ፤

ተግባር 1፡- ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የካፒታል እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ መፍቀድ እቅድ 730 ክንውን 733 አፈፃፀም 100.%፤


ተግባር 2፡- ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የግንባታ ዕቃዎች ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ መፍቀድ እቅድ 85 ክንውን 96 አፈፃፀም 112%፤

ተግባር 3፡- ተሸከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲፈቀድ ማድረግ እቅድ 23 ክንውን 34 አፈፃፀም 147%፤

ተግባር 4፡- ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መለዋወጫዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ መፍቀድ 22 ታቅዶ 21 ተከናውኗል አፋፃፀም 95%፤

ተግባር 5. የገቢ ግብር እፎይታ የድጋፍ ጥያቄ ፈቃድ መስጠት ብዛት እቅድ 82 ክንውን 86 አፈፃፀም 104%፤

3.4.3. ማምረት ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ፕሮጀክቶች ቁጥር ከ157 ወደ 250 ማሳደግ፣



ማምረት ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር

ተ.ቁ	ተግባራት	መለኪያ	የ2017 አፈፃፀም	2018 አፈፃፀም	አድገት (በመብለጥ ወይም በማነስ)
1	ከቅድመ ትግበራ ወደ ትግበራ የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች	ቁጥር	542	563	4%
2	ከትግበራ ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች	>>	157	261	66%
3	ስራ ላይ የዋለ ካፒታል	በቢ.ብር	8.25	18.65	126%
4	ለዜጎች የተፈጠረ የስራ ዕድል ብዛት	>>	6561	7611	16%

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የኢንቨስትመንት ማጠንጠኛ እና ውጤት የሆነው የፕሮጀክቶች ወደ ስራ የማስገባትና ከዘርፉ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥቅሞች ማግኘት ሲሆን በተለይ ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ከፍተኛ እድገትን ያሳያል በዚህም ጠንካራ የፕሮጀክት ክትትል ስራ እና የመረጃ አሰባሰብ ስራን በአግባቡ በመስራት የተገኘ ውጤት ነው።

3.5. የአገልግሎት አሰጣጥ እና ማበረታቻዎች አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል፣

3.5.1. የአገልግሎት አሰጣጥ ትክክለኛነትን ቁጥጥር ስራን ከ1299 ወደ 1320 ማሳደግ፣

ተግባር 1፡- ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ የተለዩ የፕሮጀክቶች መረጃ ዕቅድ በቁጥር እቅድ 1320 ክንውን 1323 አፈፃፀም 100.23%፤

ተግባር 2፡- ፕሮጀክቶችን በፋይል ቁጥጥር ማከናወን ዕቅድ በቁጥር እቅድ 1320 ክንውን 1323 አፈፃፀም 100.23%፤

(የፈቃድ አሰጣጥ፤ማበረታቻዎች አሰጣጥ፤የክትትልና ድጋፍና አሰጣጥ ቁጥጥር)

ተግባር 3፡- የፋይል ቁጥጥር ሪፖርት ማዘጋጀት ዕቅድ በቁጥር እቅድ 12 ክንውን 12 አፈፃፀም 100%፤

3.5.2. የማበረታቻ ድጋፎች ለታለመላቸዉ ዓላማ መዋላቸዉን ቁጥጥር ሽፋን ከ216 ወደ 240 ማሳደግ፣

ተግባር 1፡- በፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ቁጥጥር ስራ ማካሄድ እቅድ 240 ክንውን 242 አፈፃፀም 100.83%፤

ተግባር 2፡- ከታለመለት ዓላማ ውጪ አውለው ከተገኙ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ በመቶኛ 100% ተከናውኗል፡፡

ክፍል አራት

4. በመደመር መንግስት ዕይታ፤ የዘርፎች እመርታ በተመለከተ

- በክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር የተቀመጡ ግቦች አፈፃፀም

4.1. የመቀነስ ግቦች

መዓድ ማጋራት

የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ የውስጥ ሠራተኞችን ማዕድ ማጋራትና የሸማች ማኅበሩን ለማጠናከር በተሰራው ስራ ለተቋሙ አጠቃላይ ሰራተኞች፣ ለወላጅ አልባ ህፃናት፣ ከተቋሙ በጡረታ ለወጡ ሰራተኞችና ለአቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎች በጠቅላላው ማዕድ ማጋራት ለ400 ሰው ለማጋራት ታቅዶ ለ404 በብር 1,630,050.00 ተሰጥታ፣

ሌብነትና ብልሹ አሰራር

ከፈጻሚ

የሌብነትና ብልሹ አሰራር ውስጥ ገብተው የተገኙ 2 ፈፃሚዎች ላይ ማለትም ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ አያይዘው የተገኙት ላይ መረጃ ተጣርቶ እርምጃም ተወስዷል፡፡

ከተገልጋይ

59 ፕሮጀክቶች የወሰዱትን የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ለታቀደለት ዓላማ ባለማዋላቸው እርምጃ ተወስዷል፣

4.2. የዜሮ ግቦች

አገልግሎትን ዲጂታላይዝ በማድረግ የማኑዋል አገልግሎትን ዜሮ ለማድረግ እቅድ ተይዞ ካሉን 6 ዋና አገልግሎቶቸ እና 23 ንኡሳን አገልግሎቶች 5ቱ ብቻ በማኑዋል ሲሰሩ ሌሎቹ 18ቱ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ ናቸው፡

4.3. የአንድ ግቦች

የስማርት ኦፊስ ተጠቃሚ ለመሆን ባቀድነው እቅድ መሰረት የስማርት ኦፊስ አገልግሎት የመረጃ ልውውጦች እና የሪፖርት ቅብብሎሽ ስራን ለማቀላጠፍ እንዲረዳ የታሰበ ሲሆን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በትብብር እየሰራን አገልግሎትም እየተሰጠ ይገኛል፡፡

4.4. የሁለት ዲጂት ግቦች

ምርታቸውን ኤክስፖርት የሚያደርጉ ፕሮጀክቶችን በመለየት አስፈላጊዉን ክትትል፣ድጋፍና ማበረታቻ በመስጠት ምርታቸዉን በእጥፍ እንዲያሳድጉ ለማድረግ እየተሰራ ሲሆን የአመቱን አፈጻጸማቸውን ለማወቅ ዳሰሳ እየተደረገ ይገኛል፡፡

4.5. የ100 ፐርሰንት ግቦች

የኮሚሽኑ ሰራተኛ 100% የፋይዳ መታወቂያ እንዲያወጣ ማድረግ የሚል ግብ የያዝን ሲሆን 38 ሴት እና 58 ወንድ በድምሩ 96 ሰራተኞችና አመራሮች የፋይዳ መታወቂያ አውጥተዋል፡፡

ሚሊዮን ኮደርስ ፕሮጀክት ላይ የኮሚሽናችን ሰራተኞች እንዲሰለጥኑ ለማድረግ በታቀደው መሰረት መሰልጠን ከሚገባቸው 76 ውስጥ 73ቱ ሰልጥነዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 54ቱ (76%) ደግሞ አራቱንም ኮርስ አጠናቀዋል፡፡

4.6. በህዝብ መድረክ የተነሱ ዋና ዋና ጥያቄዎች አፈፃፀም

ወደ ትግበራ ያልገቡትን ፕሮጀክቶች ለማሰገባት ከተያዘው እቅድ አንጻር 38 ሆቴሎች ችግር ያጋጠማቸውን በመለየት ውይይት የተደረገ ሲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋርም ሁለት ጊዜ በመድረክ ንግግር በማድረግ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈራርሞ ወደተግባር ተገብቷል።

ክፍል አምስት

5. በአፈፃፀም ሂደት የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች፤ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

5.1. የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍቶተች

5.1.1. የነበሩ ጠንካራ ጎኖች

- የበጀት አመቱን የፊዚካል እቅድ በአመራር፣ በፈፃሚ፣ በባለድርሻና በተገልጋይ በማስተዋወቅና የጋራ በማድረግ በሂደትም አፈፃፀሙን በየጊዜው በመገምገም የተመራበት አግባብ በጥንካሬ የሚያዝ ነው።
- በደጋፊ ተቋማት አዲስ አበባ ምክርቤት ቋሚ ኮሚቴ፣ ፕላንና ልማት ቢሮ፣ ፐብሊክና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እንዲሁም ከንቲባ ጽ/ቤት የሚሰጡ የድጋፍ ግብረ-መልሶችን የእቅድ አካል በማድረግ የመፈፀምና የማስፈፀም ጥረቶች በጥንካሬ የሚያዝ ነው።
- አአመራር በቁርጠኝነትና በጥብቅ ዲሲፕሊን ስራዎችን በመምራት ጠንካራ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን፣ አደረጃጀቶችን፣ ተቋማዊ ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠርና ውጤታማ በማድረግ አመራር ስራዎችን የመራበት አግባብ በጥንካሬ የሚያዝ ነው።
- ተቋማዊ የአገልግሎትን ዲጂታላይዜሽንና ተደራሽነትን ለማስፋት የአንላይን አገልግሎትን በተቋሙ በራስ አቅምና በከተማ አስተዳደሩ የአንድ ሞሶብ አገልግሎት መስጠቱ፣
- የፕሮጀክቶች የመስክ ድጋፍና ክትትል በአመራር ጭምር እየተሰራ በመሆኑ የፕረጀክት አፈፃፀም በተግባር የሚጋጥሙ ችግሮች እንዲፈቱና በባለሀብቱ አመኔታ ማሳደሩ፣
- የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና የሌብነትና ብልሹ አሰራር ችግሮችን በአሰራር፣ በአደረጃጀትና በቴክኖሎጂ ለመፍታት የተመራበትና እስከ እርምጃ ድረስ የደረሰበት አግባብ፣
- ውጤታማ የተቋም በጎ አድራጎት እና ኢንሸቲቪ ሥራዎች የተመሩበትና የተገኙ ውጤቶች በአወንታ የሚያዙ ናቸው።
- ጠንካራ የኮሚኒዩኬሽንና ህዝብ ግንኙነት ስራ በተለይም መደበኛ የቴሌቪዥንና የሬድዮ ፕሮግራሞችን በመጠቀም የመረጃ ተደራሽነትንና ገፅታ ግንባታ ስራዎችን ተችሏል።
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ EQA(የጥራት ሽልማት ድርጅት) ውድድር የላቀ የመዓረግ ተሸላሚና በሀገር አቀፍ ደረጃ በተደረገ የኢንቨስትመንት ውድድር 2ኛ ደረጃ በመውጣት የኮሚሽኑን ስም እና ገፅታ ከፍ ማድረግ ተችሏል፣

5.1.2. የነበሩ ክፍተቶች

- ምርጥ ተሞክሮዎችን የመለየት የመቀመርና የማስፋት ውስንነቶች፣
- የበጀት አያያዝና የግዢ አፈፃፀም ላይ የታዩ ውስንነቶች፣

5.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

5.2.1. ያጋጠሙ ችግሮች

- የሰው ሀይል እጥረትና ለተጠየቁ የሰው ሀይል ጥያቄዎች ምላሽ አለማግኘትና የስራ ጫና፣
- በውጭ አቅም እንዲሰጡ በእቅድ የተያዙ ስልጠናዎችን ለመስጠት ከፋይናንስ አሰራር ጋር በተያያዘ መቸገር፣

5.2.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- በተደጋጋሚ መጠየቅ፣ ጊዜያዊ አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን በመውሰድ ውክልና እና ኮሚቴዎችን ጭምር በማዋቀር ለመስራት መሞከርና በዘላቂነት ከፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ ጋር በመነጋገር መፍትሄ ለመስጠት እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ስልጠናዎችን በውስጥ አቅም መስጠት

5.3. የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች

- ተቋማዊ ምቹ የስራ አካባቢን በማደራጀትና ጠንካራ የእርስ በእርስ ግንኙነት በመፍጠር የሰራተኛ እርካታን በለፈው አመት ከነበረበት 65.3 በመቶ በዚህ አመት 83.7 በመቶ ማድረስ መቻሉ እና የተገልጋይ እርካታ 94.7% ማድረሱ፤
- የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማዘመን የባለሀብቱን ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብና ሌሎችንም በመቆጠብ ስራው ላይ ብቻ እንዲያተኩር ለማድረግ በተቋሙ ከሚሰጡ አጠቃላይ 23 አገልግሎቶች 18 አገልግሎቶችን በኦንላይን መሰጠቱ፤ ጠንካራ የፕሮሚሽን ስራዎችን በመስራት 4900 አዲስ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰጠቱ፤
- ከፍተኛ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን በመስረትና 261 ፕሮጀክተችን ወድ ስራ ማስገባት መቻሉ ለ7611 ዜጎች የስራ እድል መፈጠሩና 18.65 ቢሊዮን ብር ካፒታል ስራ ላይ ማዋል የተቻለ መሆኑ፤

- የተጠናከረ የፕሮጀክት ቁጥጥር ስራን በመስራት ላልተገባ አላማ ያዋሉ 59 የፕሮጀክት ባለቤቶችን እርምጃ መወሰዱ የመንግስትና የህዝብ ቀረጥና ታክስ ማስመለስ መቻሉ፡፡

5.4. ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች፡፡

- ከበጀት አመቱ አፈፃፀም በመነሳት የቀጣይ በጀት አመት የፊዚካልና የበጀት እቅድ በአግባቡ ማቀድ፣ በየደረጃው ላለ አመራር፣ ባለሙያ፣ ባለድርሻ፣ ተገልጋይ የጋራ በማድረግ ወደስራ መግባት፣
- የጥናትና ፕሮሞሽን የስራ ክፍልን ማጠናከርና በማስተዋወቅ ኢንቨስትመንት ለመሳብ በልዩ ትኩረት እንዲሰራ ማስቻል፡፡
- የተጠናከረ የድጋፍና ክትትል ስራን በመስራት ፕሮጀክቶችን ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ በማድረግ ከተማችን ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ማስገኘት፤
- በድጋፍና ክትትል የተለዩ የፕሮጀክት ችግሮችን በሀላፊነት በመፍታት ወደስራ ያልገቡ ባለሀብቶችን ወደስራ እንዲገቡ ማድረግ ስራ ላይ ያሉትን ደግሞ በሙሉ አቅም እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተግባራትን በመለየት በቀጣይ የ3 ወር እቅድ ውስጥ ማስገባት፤

ክፍል ስድስት

ማጠቃለያ

የአ.አ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በ2018 በጀት አመት በዝግጅት ምእራፍ ያስቀመጠውን እቅድ ተከትሎ በበጀት አመቱ በዋና ዋና ስራዎች ላይ ኢንቨስትመንትን በማጥናትና በማስተዋወቅ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት፤ ለፕሮጀክቶች ጠንካራ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ፕሮጀክቶች ወደ ስራ እንዲገቡ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል። በተለይ የአገልግሎትን ተደራሽነት በማስፋት በኮሚሽኑ እና በከተማ አስተዳደሩ የአንድ ሞሶብ አገልግሎት ማዕከል በኦንላይን በመስጠት ውጤታማ መሆን የተቻለ ሲሆን በአጠቃላይ ተቋማዊ አፈፃጸም ላይ የተሻለ ውጤት ማግኘት ተችሏል።

በሌላ በኮል በተቋሙ በውጭ አቅም የሚሰጡ ስልጠናዎችን ለመስጠት እና የኢንቨስትመንት ፎረም መድረኮች ለማካሄድ የገንዘብ ወጪ የሚጠይቁ ስራዎችን ለመስራት ከፋይናንስ አሰራር ጋር በተያያዘ ለመስራት አለመቻል በክፍተት የሚያዝ ነው።

ኮሚሽኑ በበጀት አመቱ የተገኘውን ውጤት እንደ አቅም በመውሰድና ያሉትን ክፍተቶች በመሙላት የ2019 በጀት አመት እቅድ በአግባቡ በመስራት በኢንቨስትመንት ዘርፉ ለመደገፍ በሚያስችል ተቋማዊ ስነ-ልቦና በመላበስ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያሉትን ስራ የቅንጅታዊ አሰራርን አጠናክሮ በመሰራት ባለለሀብቱ ላይ የሚፈጠሩ ጫናዎችን መቀነስ፤ በበሰለ አመራር እይታ በመምራት የመልካም አስተዳር የብልሹ አሰራር ስራዎችን በመፍታት፤ ፈጣን እና ቀልጣፋ በቴክኖሎጂ የተደገፉ አገልግሎት መስጠት የቀጣይ ትኩረት ይሆናል።

ማጠቃለያ ዕቅድ አፈፃፀም ማነፃፀሪያ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
የተቋሙ ቁልፍ ተግባራት ክብደት								
1	የተቋም ግንባታና የሪፎርም ስራዎች አፈጻጸም ማሻሻል							
1.1	አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል እርካታን ማሳደግ፤							
1	በተቋም የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እንዲሰጡ ማድረግ	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
2	በአገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋሉ ሌብነትና የብልሹ አሰራር ማክሰሚያ ስርዓት በመዘርጋት መተግበር	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
	አገልግሎት በስታንዳርድ የማይሰጡ አካላትን ተጠይቂ ማድርግ	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
1.2	ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር አገልግሎቱን 100% ማሻሻል፣							
1	በተቋሙ ምቹ የመስተንግዶ ስርዓት በመዘርጋት እንግልት እንዲቀንስ ማድረግ	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
2	ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተገልጋዮች የአገልግሎት ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችሉ አማራጭ መንገድ አገልግሎት መስጠት	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
1.3	ብዙሃን መገናኛ አውታሮችን በመጠቀም የአገልግሎት ውጤታማነት ማሳደግ፣							
1	የሚዲያ ሽፋን በመስጠት የተገልጋይና የአገልጋይ መድረክ በመፍጠር እንዲሳተፉ ማድረግ	በቁጥር	-	48	48	45	94%	
2	ከተገልጋይ በተሰጡ ግብዓቶች መሰረት አገልግሎት እንዲሻሻል ማድረግ	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
1.4	ተቋማዊ አቅም ግንባታ ስርዓት በመዘርጋት የሰራተኛው የመፈጸም አቅም ማጎልበት፣							
1	ተቋማዊ የክፍተት ዳሰሳ ስራ በመስራት የሰራተኞችን የባህሪያዊና የቴክኒካል ብቃት ክፍተት መመላት	በቁጥር	1	1	1	1	100	
2	ተቋማዊ የዕውቀት አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ	በመቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
3	ወርቃማ ሰዋ/አብሮነት/ መድረክ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ማድረግ	በቁጥር	48	48	48	48	100%	
1.5	**ተቋማዊ ውጤታማነት በማሻሻል የሰራተኛና ተገልጋይ እርካታ ማሳደግ፣**							
1	የቀነሰ የተቋሙ የሰራተኛ ቅሬታ፣ (100% መቀነስ)	100%	100%	100%	100%	100%	100%	
2	የሰራተኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት መስራት (ወደ 70% ማሳደግ)	በቁጥር	1	1	1	1	100%	
3	የተቋሙ የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳ ጥናት መስራት (ወደ 93% ማሳደግ)	በቁጥር	1	1	1	1	100%	
1.6	**በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሰጡ አገልግሎቶች ውጤታማነት ማሻሻል፣**							
1.	በተቋም ደረጃ በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሠጡ አገልግሎቶች የመለየት ስራ መስራት	በቁጥር	-	16	16	18	131%	
2.	ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ ማድረግ	በቁጥር		16	16	18	131%	
2	**የከተማ መልካም አስተዳደር ችግር መፍታት፣ የአቤቱታ መወሰንና ማስፈጸም አቅም ማጎልበት እና ተቋማዊ የቅንጅት፣ የትብብርና የድጋፍ አሰራር ስርዓትን ማሻሻል፣**							
2.1.	**የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ቅሬታን የመቀነስ አሰራን ማሳደግ (ክብደት = 7)**							
1	በህዝብ የሚነሱና በየደረጃው የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና የቅሬታ ምንጮች	ቁጥር	1	1	1	1	100%	
2	የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመቶኛ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
3	በተገልጋይ ለቀረበ ቅሬታና አቤቱታ አሰራሩን ጠብቆ የተሰጠ ምላሽ በመቶኛ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
4	በተገልጋይ በአንድ ማዕከል ላይ ለቀረበ ቅሬታና አቤቱታ የተሰጠ ምላሽ በመቶኛ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
2.2.	**የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ማሳደግ፣**							
1	ለማንዛቤ እና ስርፀት የተፈጠረ መድረክ እና የተሳተፈ የሰው ኃይል ብዛት	ቁጥር	1	1	1	1	100%	
2	የተወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነት አፈፃፀም በመቶኛ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
3	በየደረጃው በአፈፃፀም ሂደት ለታዩ ችግሮች ተጠያቂነት ማረጋገጥ በመቶኛ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
2.3	**የሕዝብና፣ ሲቪል ማኅበራትና የግል ሴክተር ተሳትፎ ስርዓትን ማሳደግ፤**							
1	ተቋም ተኮር ሲቭል ማህበራት የተለዩ ብዛት	ቁጥር	1	3	3	3	100%	ሲቪል ማህበራትን ያካተተ መማክርት ጉባዔ በማቋቋም ወደተግባር ተገብቷል
2	በጋራ ፍላጎት መሠረት የተዘጋጀ መድረክና ተሳትፎ	ቁጥር	-	2	2	3	100%	
2.4	**ተቋማዊ ውጤታማነትን ማሳደግ፤ (ክብደት = 3)**							
1	በመልካም አስተዳደር ችግርና ቅሬታና አቤቱታ ምንጮች ዙርያ የተደረገ ጥናት ብዛት	ቁጥር	1	1	1	1	100%	
2	የጥናት ውጤቱ ጥቅም ላይ ለማዋል የተፈጠረ የስልጠና እና ስርፀት መድረክ ብዛት	ቁጥር	1	1	1	1	100%	
2.5	**ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት እና አተገባበርን ማሳደግ፣**							
1	በስታንዳርዱ መሰረት በተቋሙ የተለዩና በጋራ ያቀዱ ተቋማት ብዛት	ቁጥር	12	12	12	12	100%	
	እቅዱን ለማሳካት በአፈፃፀም ሂደት የተደረጉ የጋራ ግምገማዎች	ቁጥር	4	4	4	2	50%	
2.6	**የኢንሼቲቭና የሰው ተኮር ስራዎችን አፈፃፀም ማሳደግ፤**							
1	አሰራሩን ጠብቆ የተደረገ የወርቃማ ሰኞ ግንኙነት ብዛት	ቁጥር	48	48	48	48	100%	
2	የኢንሼቲቭና የሰው ተኮር ስራዎችን ውጤታማነት ግምገማ ሰነድ	1	ቁጥር	1	1	1	100	
3.	**የዕቅድ/ሪፖርት ዝግጅት፣ የኢንሸቲቭ ስራዎች አሰራር ሥርዓትን ማጎልበት፣**							
3.1	**ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ እንዲሁም ተናባቢነትን ማረጋገጥ፣**							
2	ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድ/ክለሳ ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ	ቁጥር	2	2	2	2	100%	
3	ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ	ቁጥር	12	12	12	12	100%	
	የተቋም እቅድ እና አፈጻጸም እስከ ሰራተኞች ያለው ተናባቢነት	ቁጥር	4	4	4	4	100%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
3.2	**በተቋማት የስራ አመራር ስርዓት ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=4%)**							
1	ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ለማረጋገጥ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተገኘ ውጤት፣	ቁጥር	4	4	4	4	100%	
2	በየሩብ ዓመት አፈጻጸም ከዘርፍ ጋር በጋራ ስራ መገምገም	ቁጥር	4	4	4	4	100%	
3	በተለያዩ ዘዴዎች የተቋምን እቅድና አፈጻጸም ለባለ ድርሻ አካላትና ለተገልጋይ በማስተዋወቅና ማሳተፍ፣	ቁጥር	2	2	2	2	100%	
3.3	**የተቋም በጎ አድራጎት እና ኢንቨቲቪ ሥራዎችን ማጎልበት፣**							
1	የአቅመ ደካማ ቤተሰቦችን ቤት ማደስ	ቁጥር	1	3	3	3	100%	
2	የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከልና መንከባከብ	ቁጥር	1500	2000	2000	2050	+100%	
3	ወላጆቻቸውን ያጡ ወይም የገቢ አቅማቸው ደካማ የሁኑ ወላጆች ሥር የሚተዳደሩ ህፃናትን መደገፍ	ቁጥር	3	3	3	4	+100%	
4	ማዕድ ማጋራት (ለማህበረሰብ እና ለሠራተኛ)	ቁጥር	327	400	400	407	+100%	
4.	**የጥናት እና የፕሮሞሽን ስራዎችን በማጠናከር የኢንቨስትመንት ፍሰትን መጨመር፣**							
4.1.	የኢንቨስትመንት አማራጭ ጥናቶችን ወደ 5 በማሳደግ፣ ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ (ክብደት=5%)							
1	የከተማዋን አማራጭ የኢንቨስትመንት መስኮችን በጥናት በውጭ አቅም /አውትሶርስ/ መለየት፣	ቁጥር	-	1	1	1	100%	
2	የተለያዩ ርዕስ ያላቸው የኘሮጀክት ኘሮፋይሎችን በውስጥና በውጭ አቅም /አውትሶርስ/ ማሰራት፣	ቁጥር	-	10	10	4	40%	ስራውን ለመስራት ተጫራች ባለመቅረቡና ሁለተኛ አማራጭ በውስን ጨረታ ለማሰራት የግዢ መመሪያው ከዚህ በላይ ለመስራት ስለማይፈቅድ
3	ችግር ፈች ጠናቶች በራስ አቅምና በውጭ አቅም /አውትሶርስ/ ማሰራት፤	ቁጥር	2	2	2	2	100%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
4	የደንበኛ እና የሰራተኛ የእርካታ ደረጃ የሚያመለክት ጥናት ማጥናት፣	ቁጥር	2	2	2	2	100%	
4.2.	**የተጠናከረ የፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት የኢንቨስትመንት ፍሰትን መጨመር፣**							
1	አንድ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣	ቁጥር	-	1	1	1	100%	
2	በራስ አቅምና በተዘጋጁ ኤግዚብሽኖች ላይ በመሳተፍ ኢንቨስትመንትን ማስተዋወቅ	ቁጥር	4	4	4	4	100%	
3	ለደንበኞች የምክር እና መረጃ አገልግሎት መስጠት፣	ቁጥር	4215	4,300	4,300	4323	103.8%	
4	በህትመት የማስታወቂያ ዘዴዎች የብራንድ እና የገጽታ ግንባታ ስራ መስራት	ቁጥር	7753	5500	5500	5500	100%	
5	ከአጋር አካላት ጋር የኢንቨስትመንት ፎረም ማዘጋጀት	ቁጥር	-	2	2	-	0	ሆቴሎችና አዳራሾች ከወጪ ቅነሳ የከተማ አስተዳደሩ የፋናንስ መመሪያ አንፃር ክልከላ በመደረጉ ያልተሰራ
6	በኢንቨስትመንት አማራጭ እና ማበረታቻ ዙሪያ የኢንቨስትመንት የግንዛቤ እና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣	ቁጥር	2	2	2	2	100%	
5.	**ቀልጣፋ ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶችን ማሳደግ፣**							
5.1.	**የኢንቨስትመንት ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶችን ወደ 6160 ማሳደግ፣**							
1	ለባለሀብቶች አዲስ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት	ቁጥር	3383	3500	3500	4900	140%	የኦንላይን አገልግሎት በመጀመሩን የፕሮሞሽን ስራ በመስራቱ
2	ለባለሀብቶች ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት	ቁጥር	275	280	280	346	124%	
3	ለባለሀብቶች ለውጥ /ማሻሻያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት	ቁጥር	373	380	380	329	87%	
4	ለባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት መስጠት	ቁጥር	1948	2000	2000	1332	67%	
5	ለባለሀብቶች ኢንቨስትመት ፈቃድ ስረዛን መስጠት	በ%	100%	100%	100%	100%	100%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
6	ከኢንቨስት ፈቃድ ነክ፣ ማበረታቻና ሌሎች ድጋፎች የሚገኝ ገቢን መሰብሰብ፤	በሚ/ብር	32.7	36	36	36.2	100.2%	
5.2.	**የዉጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ለሥራ ፈቃድ ጥያቄ ምላሽ መስጠት፣**							
1	ለየዉጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ለሥራ ፈቃድ ፈላጊዎች ድጋፍ ማድረግ	ቁጥር	139	140	140	114	81%	
2	ለዉጭ ዜጋ ቀጣሪዎች መድረክ በማዘጋጀት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መገምገም	ቁጥር	-	4	4	4	100%	
3	ለዉጭ ዜጋ ቀጣሪዎች በመስክ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣	ቁጥር	-	4	4	4	100%	
5.3.	**የጥሪ ማዕከልና መዝገብ ቤት አገልግሎት ማሻሻል (ክብደት=1%)**							
1	የተሰረዙ ፋይሎችን ማደራጀትና ለወመዘክር ማስረከብ	ቁጥር	-	25 ሺ	25 ሺ	15000	-	ፋይል የመለየት ስራው ተሰርቶ ለርክክብ ከወመዘከር ጋር በንግግር ላይ ያለ
2	የስልክ ጥሪ ማዕከል ማቋቋም	ቁጥር	-	1	1	-	-	በሂደት ላይ ያለ
6.	**የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመረጃ ጥራት፣ የክትትልና ድጋፍ ሽፋን ማሳደግ**							
6.1.	**አዲስ እና ነባር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመረጃ ጥራት 100% ማሳደግ፣**							
1	የተደራጀ አዲስ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መረጃ	ቁጥር	2684	4719	4719	4683	99%	
2	የተደራጀ ነባር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መረጃ	ቁጥር	17971	19,000	19,000	19000	100%	
6.2.	**በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ላይ የክትትል ሽፋን ከ20,999 ወደ 27,071 ማሳደግ፤**							
1	በሚቀርቡ አዲስ የሶስት ወርና የስድስት ወር የፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ የሚደረግ ክትትል	ቁጥር	2,941	4719	4719	4683	99%	
2	የአፈፃፀም ደረጃቸውን ለመለየት የመደበኛ ክትትል የሚደረግባቸው ነባር ፕሮጀክቶች	መቶኛ	17971	19,000	19,000	19000	100%	
3	በትግበራ ላይ ያሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ችግር ፈቺ ድጋፍ መስጠት የሚያስችል የመስክ ክትትል	ቁጥር	2679	2456	2456	2494	102%	
4	በሆቴል፣ ቱሪዝምና አይሲቲ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የክትትል ድጋፍ	ቁጥር	-	146	146	146	100%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
5	በኤክስፖርት ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የክትትልና ድጋፍ	ቁጥር	71	100	100	100	100%	
6	ተኪ ምርቶች ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚደረገውን የክትትል ድጋፍ	ቁጥር	-	650	650	666	102%	
7.	ስትራቴጂክ ግብ 7. ለፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ የድጋፍ ስርዓት መዘርጋት፣							
7.1.	ዓላማ 1. የድጋፍና የማመቻቸት ተግባር (facilitation) ውጤታማነትን 100% ማድረስ፣							
1	የፋይናንስ፣ የብድር እና የውጭ ምንዛሬ ድጋፍ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ማድረግ፣	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
2	የመሰረተ ልማት ድጋፍ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ማድረግ፣	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
3	ቀረጥ ከፍለው የሚገቡ ዕቃዎችን ለማስገባት ለሚቀርብ ጥያቄ ድጋፍ ማድረግ	መቶኛ	100%	100%	100%	100%	100%	
4	የቴክኒክ ድጋፍ የተደረገላቸው ፕሮጀክቶች ብዛት	ቁጥር	26	35	35	33	94.3%	
5	ከአካበባቢ ጋር የሚኖራቸው ተስማሚነት የተረጋገጠላቸው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች	ቁጥር	18	20	20	20	100%	
6	በድህረ- ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ተለዩ ፕሮጀክቶች	ቁጥር	22	32	32	32	100%	
7.2.	የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ፍቃድ እና የገቢ ግብር እፎይታ ድጋፍ ወደ 1260 ማሳደግ፣							
1	የካፒታል እቃዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲፈቀድ ማድረግ፤	ቁጥር	946	950	730	733	100%	
2	የግንባታ እቃዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲፈቀድ ማድረግ፤	ቁጥር	127	130	85	96	112%	
3	ተሸከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲፈቀድ ማድረግ፤	ቁጥር	19	20	23	34	147%	
4	መለዋወጫ እቃ ከቀረጥ ነጻ እንዲፈቀድ ማስቻል፤	ቁጥር	37	40	22	21	95%	
5	የገቢ ግብር እፎይታ እንዲፈቀድ ማድረግ፤	ቁጥር	114	120	82	86	104%	
7.3.	ማምረት ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ፕሮጀክቶች ቁጥር ከ157 ወደ 250 ማሳደግ፣							
1	ከቅድመ ትግበራ ወደ ትግበራ የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች	ቁጥር	542	550	550	568	102%	
2	ከትግበራ ወደ ማምረትና አገልግሎት መስጠት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች	ቁጥር	157	250	250	261	104%	

ተ.ቁ	ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች	መለኪያ	2017 አፈፃፀም	2018 ግብ	የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም			ለእቅድ አፈጻጸም ከፍተኝነት /ዝቅተኝነት ማብራሪያ
					እቅድ	ክንውን	አፈፃፀም በ%	
3	ስራ ላይ የዋለ ካፒታል በቢሊ ብር	በቢ. ብ	8.25	10	10	18.65	187%	ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ መረጃ የማሰባሰብ ስራ በመሰራቱ
4	ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች የፈጠሩት የስራ ዕድል በቋሚ	ቁጥር	6561	7500	7500	7611	101%	
8.	ስትራቴጂክ ግብ 8. የአገልግሎት አሰጣጥ እና ማበረታቻዎች አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል፣							
8.1.	የአገልግሎት አሰጣጥ ትክክለኛነትን ለማረጋጋጥ የሚሰሩ ቁጥጥር ስራዎችን ከነበረበት 1296 ወደ 1320 ማሳደግ፣							
1	ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ የተለዩ የፕሮጀክቶችን መረጃ ማደራጀት፤	ቁጥር	1296	1320	1320	1323	100.23%	
2	ፕሮጀክቶችን በፋይል ቁጥጥር ማከናወን፣	ቁጥር	1296	1320	1320	1323	100%	
3	የፋይል ቁጥጥር ሪፖርት ማዘጋጀት ዕቅድ በቁጥር 12፣	ቁጥር	12	12	12	12	100%	
8.2.	የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ድጋፎች ለታለመላቸዉ ዓላማ መዋላቸዉን ቁጥጥር ከነበረበት 216 ወደ 240 ማሳደግ፣							
1	ፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ቁጥጥር ስራ ማካሄድ	ቁጥር	216	240	240	242	100.83%	
2	ከታለመለት ዓላማ ውጪ አውለው ከተገኙ እርምጃ እንዲወሰድየውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ	በ%	100	100%	100%	100%	100%	